# የሻማ መብራት ስነሥርአት መካሄድና ብርቱካንን የማስፈታት ዘመቻ መጀመር

የፐርዝ ከተማ ኗሪ የሆኑ ኢትዮጵያውያን ማክሰኞ ዲሴምበር 23 ቀን 2009 በምእራብ አውስትራሊያ መስተዳድር፤ የአምነስቲ ኢንተርናሽናል ጽሕፈት ቤት የሻማ ማብራት ምሽት በማካሄድና፤ በርቱካንን እና ሌሎች የፖለቲካ እስረኞችን ለማስፈታት በዓለም ዙሪያ ከተጀመረው እንቅስቃሴ ጋር የተቀናጀ ዘማቻ በመክፈት የተሳካ ዝግጅት አካሂደዋል።



ብርቱካን ሚደግሳ የታሰረችበትን አንደኛ ዓመት ምክንያት በማድረግ በተካሄደው በዚሁ ዝግጅት ላይ፤ በወያኔ አገዛዝ እስር ቤቶች የሚማቅቁትን የፖለቲካ እስረኞች ሁሉ በማሰብ የአንድ ደቂቃ የህሊና ፀሎት ተደርጓል።

በዚሁ ጊዜ የምእራብ አሰስትራሊያ መስተዳድር የአምኔስቲ ኢንተርናሽናል ፕሬዚዳንት ሚስተር ግሬግ ስቲት፤ አምኔስቲ ኢንተርናሽናል በርቱካንን ለማስፈታት በዓለም ዙሪያ የጀመረውን እንቅስቃሴ ዘርዝረው፤ በአውስትራሊያም ተመሳሳይ ዘመቻ የሚካሄድ መሆኑ አስታውቀዋል።

የመስተዳድሩ የአንድነት የድጋፍ ኮሚቴ ሰብሳቢ በበኩላቸው ባደረጉት ገለጻ፤ በኢትዮጵያ አምባገነን መሪዎች የፖለቲካ ተቀናቃኞቻቸውን ለማስወገድ የሚፈጽሙት ጭካኔ የቆየ ታሪክ ያለው መሆኑን አውስተው፤ ወያኔ ብርቱካንን በኢትዮጵያ ሕዝብና በዓለም አቀፉ ሕብረተሰብ ተገዶ መፍታት እንደሚኖርበትና ለዚህም የተጠናከረ ዘመቻ ማካሄድ ግድ እንደሚል አመልክተዋል።

ብርቱካንን ለማስፈታት በዓለም አቀፍ ደረጃ የተቋቋመው ግብረሃይል የአውስትራሊያ አስተባባሪ በበኩላቸው፤ ግብረሃይሉ ያከናወናቸውን ተግባሮችና ለማከናውን ያቀዳቸውን ሥራዎች ለታዳሚዎቹ አስረድተዋል።

በዚሁ ጊዜም፤ የሰነሥራአቱ ተካፋዮች ለአውስትራሊያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትርና ለተቃዋሚው ፓርቲ አቻቸው እንዲሁም ለአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር፤ ለኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይና የፍትህ ሚኒስትሮች በየበኩላቸው ብርቱካን እንድትፈታ ለማድረግ እንዲተባበሩ የሚጠይቁ ደብዳቤዎች ልከዋል።

በመጨረሻም፤ ተካፋዮቹ በርቱካንን እና ሌሎች የፖለቲካ እስረኞችን ለማስፈታት የሚካሀደውን ዘመቻ በተጠናከረ ተሳትፎ ለመቀጠል ቃል በመግባት የእልቱን ክንዋኔ አጠናቀዋል።

የምዕራብ አውስትራሊያ የአንድነት ፓርቲ የድጋፍ ቡድን

24 ዲሴምበር 2009